# ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ




ወልደ ነጐድጓድ በመባል ተለይቶ የታወቀው ዮሐንስ የዘብዴዎስ ልጅ የያዕቆብ ወንድም ነው ። ለሐዋርያነት ከመጠራቱ በፊት ዓሣ አጥማጅ ነበር ። ዓሣ ከማጥመድ ሥራውም ጋር የመጥምቁ ዮሐንስን ትምህርት ይከታተል ነበር ። በግልጥ አነጋገር የዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበር ለማለት ይቻላል ።

አንድ ቀን ዓሣ በማጥመድ ሥራው ላይ እንዳለ የጌታችን የኢየሱስክርስቶስ ጥሪ ደረሰው ። ወዲያውም ሁሉን ነገር ትቶ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ሆነ ትውፊት እንደሚያስረዳን ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ከአራቱ ወንጌላት አንዱን የመጨረሻውን ወንጌል ከሰባቱ መልአክታት ሦስቱን መልእክታትና መጽሐፈ ራእይን ጽፎአል ። ዮሐንስ ከሦስቱ ቀራቢዎች ወይም ምሥጢራውያን ደቀ መዛሙርት አንዱ ነው ። እነርሱም ጴጥሮስ ያዕቆብና ዮሐንስ ናቸው ። ምሥጢራውያን መባላቸውም ሀ ጌታ የኢያኢሮስን ሴት ልጅ ከሞት ባስነሣ ጊዜ ለ በደብረ ታቦር ምሥጢረ መለኮቱን በገለጠ ጊዜ ሐ በጌቴሴማኒ በጸለየ ጊዜ እነዚህ ሦስቱ ደቀመዛሙርት ብቻ አብረውት ነበሩ ።

ዮሐንስ በግብሩና በጠባዩ በተለያየ ቅጽል ስሞች ይጠራል ። ለምሳሌ ቁጡና ፈጣን ስለነበር ወልደ ነጐድጓድ እንደተባለ በሊቃውንት ይተረጐማል ። በተጨማሪም ነጐድጓድ መደንግፅ እንደ ሆነ ዮሐንስም መደንግፀ መናፍቃን በመሆኑ ወልደ ነጐድጓድ እንደተባለ የተረጐሙ ሊቃውንት አሉ ። (ማር. 9 ፡ 38 - 39 ሉቃ. 9 ፡ 54)

ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ (የጌታ ወዳጅ) በመባል ይጠራል ። እንደዚሁም የፍቅር ሐዋርያ ይባላል ይህ ስያሜ ዮሐንስ ስለ ክርስቲያናዊ ፍቅር በብዛት ከመጻፉ በላይ ‘‘እግዚአብሔር ፍቅር’’ እንደሆነ ደጋግሞ መጻፉን ያመለክታል ።

እርግጥ ፍቁረ እግዚእ’’ በመባል የሚጠራው ደቀ መዝሙር ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ መሆኑ እስከ አራተኛው ምእት ዓመት ገደማ ድረስ አልታወቀም ነበር ። ምክንያቱም አራተኛው ወንጌል ፍቁረ እግዚእ ወይም ጌታ የሚወደው ደቀ መዝሙር ብቻ ይላል እንጂ ስም ለይቶ አይጠራም ። ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም አንዳንዶቹ ፍቁረ እግዚእ የተባለ ማርቆስ የተሰኘው ዮሐንስ እንጂ የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ እንዳይደለ ተናግረዋል ጽፈዋልም ። (አውሳብዮስ የቤ ክ. ታሪክ 6 ፡ 25 ።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ መልአከ ፀሐይ ተገኝም ‘‘ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት ። ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን እናትህ እነኋት አለው ። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ወደቤቱ ወሰዳት-ዮሐ 19፡26-27)የሚለውን ንባብ ለቅዱስ ማርቆስ ሰጥተው ተርጉመዋል ። ምክንያቱን ሲገልጡ በኢየሩሳሌም ውስጥ የቅዱስ ማርቆስ የእናቱ ቤት ነበር እመቤታችንም ከዕለተ ዐርብ እስከ በዓለ ሃምሳ በቅዱስ ማርቆስእናት በማርያምቤት ነበረችለዮሐንስወልደ ነጐድጓድግን በገሊላእንጂ በኢየሩሳሌምቤት አልነበረውም ስለዚህ ‘‘ወደቤቱ የወሰዳት ደቀመዝሙር ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ጽፈዋል (የሐዋ.1 ፡ 12-14 12 ፡ 12 )

በኋላ ግን በአምስተኛው ምእትዓመት ገደማ ልክ ዛሬ እንደሚታመነው ፍቁረ እግዚእ ወይም ጌታ የሚወደው ደቀ መዝሙር የተባለ ዮሐንስ (የዘብዴዎስ ልጅ) ወልደ ነጐድጓድ እንደሆነ ተረጋገጠከዚህምየተነሣ በመጨረሻ ራት ጊዜ በጌታ አጠገብ ተቀምጦ የነበረው ደቀ መዝሙርዮሐንስነውእነኋትእና



www.ethiopianorthodox.org

ትህ እነሆ ልጅሽ ተብሎ የተነገረለት
ደቀ መዝሙርም ዮሐንስ ነው ።

በትንሣኤ ሌሊትም ከጴጥሮስ ጋር
ወደ ጌታ መቃብር የሮጠው ደቀመዝ
ሙር ይኸው ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ
እንደሆነ ቤ ክርስቲያን አረጋግጣ ተቀ
በለች ከዕርገት በኋላ ዮሐንስ በኢየሩሳ
ሌም ከጴጥሮስ ጋር ታላላቅ ሥራዎችን
ሠርቷል በሐዋርያት ሥራ 3 ፡ 1 እና
11 ላይ እንደተገለጠ ሽባውን ሰው በጌታ
ስም አድኖአል ። በሕዝብና በሊቃነ
ካህናት ፊት ከሙታን ተለይቶ ስለተነሣ
ክርስቶስ ከጴጥሮስ ጋር በግልጥ መስ
ክሮአል (የሐዋ.4 ፡ 1 - 21) የሰማርያ
ሰዎች አምነው ከተጠመቁ በኋላ መን
ፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ቅዱስ ዮሐንስ
ከጴጥሮስ ጋር ጸለየላቸው (የሐዋ.8 ፡ 14)
ለመጀመሪያ ጊዜ በኢየሩሳሌም በተደ
ረገው ሲኖዶስ ዮሐንስ ተገኝቷል የሐዋ.
15 ።

ዮሐንስ በመጨረሻ ጊዜ ወደ ትንሹ
እስያ ሄዶ በኤፌሶን ከተማ ይኖር ነበር
ኤፌሶን በአሁኑ ጊዜ በቱርክ ውስጥ
ይገኛል የክርስትና ምልክቱ ግን ጠፍ
ቷል ። ዮሐንስ በኤፌሶን ሳለ ዶምጥያን
የተባለው መሪ በፍጥሞ ደሴት አጋዘው
በዚያም ሳለ ራእዩን ጻፈ እንደገናም
በአርባ ዘመን ወደ ኤፌሶን ተመልሶ
ወንጌሉንና ሦስቱን መልእክታት ጻፈ ።

ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ከሌሎች
ሐዋርያት ሁሉ በፊት እንደተጠራ ከሐዋ
ርያት ሁሉ በኋላ የሞተ መሆኑን የቤተ
ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ። ነገር ግን
ዮሐንስ እንደ አልሞተና እስካሁን
ድረስ ከገጸ ሞት ተሰውሮ እንደሚኖር
የሚተርኩ አንዳንድ ሊቃውንት አሉ ።
እነርሱ መነሻ ያደረጉት በአራተኛው
ወንጌል በምዕራፍ 21 ፡ 21 - 24 በስም
ስለ አልተገለጠው ደቀመዝሙር የተጻ
ፈውን ዐረፍተ ነገር ነው ። ነገር ግን
ጥቅሱ "ጌታችን ኢየሱስ እስክመጣ
ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግ
ዶህ አለ እንጂ አይሞትም" አላለም ።

ስለዚህ ብዙዎቹ የቤ ክ ታሪክ ጸሐፊ
ዎች "ዮሐንስ አይሞትም" የሚለው
ዜና በኋላ እንደተጨመረ ይናገራሉ ።
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ
ክርስቲያን ሊቃውንትም ስለዚህ አስተ
ያየታቸውን ሲሰጡ ከዮሐንስ ወንጌል
21ኛውን ምዕራፍ አብሮ ኮሮስ የተባ
ለው የዮሐንስ ደቀ መዝሙር እንደጻፈ
ው ይተርካ ሉ ። በዚህ አንጻር "ዮሐንስ
አልሞተም" የሚለው ዜና የወጣ ከአብ
ሮኮሮስ ነው ። ለዚህም ሀሳብ መሠረቱ
"የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪ
ያዩ ድረስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን
የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ" ማቴ.16 ፡
28) የሚለው ጥቅስ ነው ለዚህም
የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ይችላል ።
ለምሳሌ በመንግሥቱ ሲመጣ ማለት
በደብረ ታቦር ምሥጢረ መንግሥቱን
ሲገልጥ እስኪያዩ ድረስ የማይሞቱ አሉ
ማለት ነው ብለው የሚተረጉሙ አሉ ።
ከዚህም ሌላ በዕለተ ትንሣኤ ተነሥቶ እ
ስኪያዩት ድረስ ማለት እንደሆነ የሚመ
ለከቱ አሉ ። ሌሎች ደግሞ በትክክል በዕ
ለተ ምጽአት በግርማ መንግሥት ሲመጣ
እስኪያየው ድረስ ዮሐንስ ወልደ ነጎ
ድጓድ ሞትን አይቀምስም ማለት እንደ
ሆነ ይተረጉማሉ ይሁን እንጂ አብዛኛ
ዎቹ የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት ዮሐንስ
አልሞተም በሚለው ሀሳብ አይስማሙ
ም ። ግን በ90 ዓመት ዕድሜው እንደ
ሞተ ያምናሉ ።

ያም ሆነ ይህ ዮሐንስ ዛሬ በሥጋ
ሳይሆን በመንፈስ ሕያው ነው በሥራው
ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ይኖራል ምሥ
ጢረ መለኮትንና ምሥጢረ ሥጋዌን
አምልቶና አጉልቶ የጻፈ ታላቅ ሐዋርያ
ነውና ከዚህም የተነሣ "ዘንስር ዮሐንስ"
ይባላል ። በቤተ ክርስቲያን የሥዕል
ዓለም ንስር በአጠገቡ እንዳለ ሆኖ ይሣ
ላል ። ይህም መጥቆና ረቅቆ የሚያስብ
ልዑል ስብከት መሆኑን ያመለክታል ።
ዮሐንስ በሸምግልናው ጊዜ ሁሉ የሚያስ
ተምረው ትምህርት "ልጆቼ እርስበርሳ
ችሁ ተፋቀሩ" የሚለው ቃል ነበር ደቀ
መዛሙርቱም አባታችን ለምን ሁል
ጊዜ አንድ ዓይነት ትምህርት ታስተም
ራለህ? ሲሉት "ልጆቼ ይህ የጌታ ትእዛዝ
ነው" በማለት ይመልስላቸው ነበር ።
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ
ክርስቲያን ይህን ታላቅና ተወዳጅ ሐዋ
ርያ በየዓመቱ ጥር 4 ቀን በታላቅ መን
ፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ።
በዚሁ ዕለት በስሙ በታነፁ አብያተ
ክርስቲያናት ሁሉ ያስተማረው ትምህ
ርት ያደረገው ምግባርና ትሩፋት ይታወ
ሳል ። ጥር አራት ቀን ቅዱስ ዮሐንስ
ወልደ ነጎድጓድ ከዚህ ዓለም በሞት
የተለየበት መሆኑን ከኢትዮጵያ ሊቃው
ንት ብዙዎቹ ያምናሉ ።

ሰዩፈ ሥላሴ ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org